# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ብርሃናችንን የሚነጥቁ እጆች

ተሾመ በላይ - (ከኢ.ኤ.ኃ.)

ከጊዜ ወደ ጊዜ የዓለማችን የአኗኗር ዘይቤ እየተለወጠ በመምጣቱ የሰው ልጅ አዳዲስ የኑሮ ዘይቤን እንዲከተልና እንዲላመድ አድርጎታል። ለዚህም ዋና ምክንያቱ የኢንዱስትሪ መስፋፋት እንደሆነ የተለያዩ ጥናቶች ያመለክታሉ። ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች የሰውን ልጅ ኑሮ ቀላልና ምቹ እንዲሆን አድርገዋል። ለኢንዱስትሪ መስፋፋት ደግሞ የኤሌክትሪክ ኃይል ግንባር ቀደምትነቱን ይይዛል።

ኤሌክትሪክ ከሰው ልጅ ጋር ጥብቅ ቁርኝትን እየፈጠረ በመምጣቱ ምክንያት ሀገራት በዜጎቻቸው የሚነሳውን የኃይል ፍላጎት ለማሟላት ዘርፍ ብዙ ተግባራት እያከናወኑ ይገኛሉ። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በሀገራችን ኢትዮጵያ የኃይል ፍላጎት ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ በመምጣቱ ይህን አዳጊ ፍላጎት ለማሟላትና ጥያቄውን ለማስተናገድ እንዲያስችል የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል የተለያዩ ሥራዎችን ሲያከናው ቆይቷል፤ እያከናወነም ይገኛል።

የኃይል ዘርፍ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የሚጠይቅ ቢሆንም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የሀገሪቱን የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ሽፋን ለማሳደግ በትኩረት እየሠራ ይገኛል። ይሁንና በኤሌክትሪክ ኃይል መስመር ተሸካሚ የብረት ማማዎች ላይ የሚከናወኑት የስርቆትና የዘረፋ ወንጀሎች በተቋሙ ላይ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ከማድረሳቸው ባሻገር በኅብረተሰቡ ላይም የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ አስከትለዋል። በአንዳንድ አካባቢዎች የሚፈፀመው ስርቆት ኃይል እንዲቋረጥ በማድረግ ለሀገር ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋፅዖ በሚያበረክቱ ግዙፍ ፋብሪካዎች እንቅስቃሴና ምርት ላይም ከፍተኛ ጫና እየፈጠረ ይገኛል።

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የመጣው የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ስርቆትና ውድመት ተቋሙን ምን ያህል ለኪሳራ እየዳረገው እንደሆነ የ2014 በጀት ዓመቱን ብቻ መመልከት የጉዳዩን አሳሳቢነት ለመረዳት ያስችላል። በተለይም በከፍተኛ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር ተሸካሚ የብረት ማማዎች ላይ በተፈፀመ የስርቆት ወንጀል 756 ቶን ብረት የተዘረፈ ሲሆን የኮንዳክተርን ስርቆት ጨምሮ በገንዘብ ሲተመን በተቋሙ ላይ የ100 ሚሊዮን ብር ጉዳት ከማድረሱ ባሻገር በዓመት ውስጥ ሁለት ሺህ 396 ጊጋ ዋት ሰዓት ኃይል እንዳይሸጥ በማድረግ ተቋሙ ላይ ጉዳት አድርሷል።

የክፍለ አህጉሩን የኃይል ትስስር በማሳደግና የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት በኩል ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይኖረዋል ተብሎ የሚታመነው የኢትዮ-ኬንያ ባለ 500 ኪሎ ቮልት ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መስመርም ስርቆት ከተፈፀመባቸው የተቋሙ መሠረተ ልማቶች ውስጥ አንዱ ነው። ይህ የከፍተኛ የኃይል ማስተላለፊያ መስመር በይፋ ሥራ ከመጀመሩ በፊት 105 ቶን በሚሆን የተለያየ ብረት፣ ስድስት ኪሎ ሜትር የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ ሽቦዎች፣ 12 ነጥብ አንድ ኪሎ ሜትር የዳታ ሲግናል ማስተላለፊያ የኦፕቲካል ግራውንድ ኬብል፣ 13 የኦፕቲካል ፋይበር ማገናኛ ሳጥኖች ላይ ስርቆት ተፈፅሞባቸዋል። በአጠቃላይ በኢትዮ-ኬንያ ባለ 500 ኪሎ ቮልት ከፍተኛ የኃይል ማስተላፊያ መስመር ፕሮጀክት ላይ የደረሰውን ስርቆት በአዲስ ለመተካት ለዋሉት ዕቃዎችና ለጥገና ከ16 ሚሊዮን በላይ የቻይና ዩዋን እና ከ20 ሚሊዮን ብር በላይ ተቋሙ ለተጨማሪ ወጪ ተዳርጓል።

የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ስርቆትና ውድመት በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች በሚባል ደረጃ እየተበራከተ የመጣ ሲሆን በተለይ በሲዳማ፣ በደቡብ፣ በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ አልፎ አልፎም በሐረሪና በሶማሌ ክልሎችና በአዲስ አበባ ዙሪያ ባሉ አካባቢዎች በሚገኙ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችና የምሰሶ አካላት ላይ ተደጋጋሚ የስርቆት ወንጀል ይፈፀማል። በከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችና ተሸካሚ ምሰሶዎች ላይ በሚደርሰው ስርቆት ምክንያት የኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚቋረጥ በመሆኑ መስመሮቹን ጠግኖ ወደ ሥራ ለማስገባት ቀናትን ይወስዳል። ይህም ኅብረተሰቡን ለተጨማሪ እንግልትና ስቃይ እንዲሁም ለመልካም አስተዳደር ችግር የሚዳርግ ይሆናል።

በየጊዜው የሚፈጸሙ የስርቆት ወንጀሎችን ለመከላከል በተቋሙ የበላይ አመራሮችና ሪጅኖች አማካኝነት ለክልል፣ ለዞንና ለወረዳ አመራሮች የኤሌክትሪክ ኃይል መሠረተ ልማቶችን ኅብረተሰቡ በባለቤትነት ስሜት እንዲጠብቃቸው ለማድረግ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛል። በተለይም ከአማራ፣ ከኦሮሚያ፣ ከሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ከፍተኛ አመራሮች ጋር ስለ መሠረተ ልማት ስርቆት በሀገርና በተቋም ላይ እየደረሰ ያለውን ኪሳራ በማሳየት ውይይት ተደርጓል። በቀጣይም በሁሉም ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችን፣ የሀይማኖት አባቶችን፣ የሀገር ሽማግሌዎችንና ወጣቶችን በማሳተፍ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች የሚሠሩ ይሆናል።

በአንዳንድ አካባቢዎች በተጀመሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ተስፋ ሰጪ ውጤቶች እየተመዘገቡ መጥተዋል። በተለይም በአማራ ክልል ወንጀሉን ለመቆጣጠር የሚሠራ ዐቢይ ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ተግባር እንዲገባ መደረጉ፣ በኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞን ሰኮሩ ወረዳ፣ በምዕራብ አሩሲ ዞን ሻሸመኔ ዙሪያ የፀጥታ አካላትን፣ የወረዳና የቀበሌ አመራሮችን፣ ነዋሪዎችን ያሳተፈ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ በመሠራቱ ማኅበረሰቡ በስርቆት ወንጀሉ የተሳተፉትን ለሕግ አካላት ጥቆማ እየሰጡ መምጣታቸው እንደ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

በአጠቃላይ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በሚገኙ የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማቶች ላይ የሚፈፀሙ ስርቆቶችን መከላከል ለመንግሥት አካላት ብቻ የሚተው ባለመሆኑ መላው ኅብረተሰብ፣ በየደረጃው ያሉ የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ እና የቀበሌ አመራሮች "በያገባኛል" ስሜት መሠረተ ልማቶችን የመጠበቅ፣ ወንጀለኞችን ተከታትሎ የመያዝ፣ የማጋለጥና ለሕግ የማቅረብ ሥራ ሊሠሩ ይገባል። በተጨማሪም የግልም ሆነ የመንግሥት ሚዲያዎች በየጊዜው በሚደርሱ የኃይል መሠረተ ልማቶች ስርቆትና ጉዳቶች ተጎጂ የሚሆነው ኅብረተሰቡ በመሆኑ በዜና፣ በፕሮግራሞቻቸውና በአምዶቻቸው ለኅብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ መልዕክቶች በማስተላለፍ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል መልዕክቱን ያስተላልፋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ